የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት አካል የውሳኔ ቁጥር 009/2018 ዜና

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት በትርታ ኤፍ ኤም ጣቢያ ላይ በቀረበ የቀጥታ ስርጭት የስነ-ምግባር ጥሰት ቅሬታን መርምሮ ውሳኔ አሳለፈ።

(የኢመብም፤ አዲስ አበባ) የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት አካል (Complaint panel) በትርታ ኤፍ ኤም የሲዲ ስፖርት የቀጥታ ፕሮግራም ላይ መጋቢት 01 ቀን 2018 ዓ.ም. በቀረበ የአድማጭ የስነ-ምግባር ጥሰት ቅሬታን መርምሮ ውሳኔ አሳለፈ።

የምክር ቤቱ የግልግል ዳኝነት በጣቢያው የቀጥታ የስፖርት ስርጭት ላይ ለህብረተሰቡ ስስ የሆኑ ጉዳዮች (ዘር፤ ብሔር፤ ኃይማኖት) ገለፃ ላይ ከፍ ያለ ጥንቃቄ መወሰድ እንዳለበት በማመን ጣቢያው ምላሽ እንዲሰጥበት ደብዳቤ መላኩን ገልፆ ጣቢያው ለቅሬታው የሰጠውን ምላሽ የመረመረ ሲሆን የጣቢያው ስራ አስኪያጅም ከአድማጭ ለቀረበው ቅሬታ ምላሽ በደብዳቤ ከመስጠታቸውም በላይ የግልግል አካሉ ቅሬታዎችን በሚመረምርበት ጊዜ በአካል ቀርበው ስለ ቅሬታው የሰጡትን ማብራሪያ አዳምጧል።

የግልግል ዳኝነት አካሉ (Complaint panel) በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ጣቢያው ለቅሬታው ምላሽ እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበው የተፈፀመው የሚዲያ ስነ ምግባር እጅግ ግዙፍ የሙያ ጥሰት ሆኖ ሳይሆን በተለይ ኃይማኖት ነክ ጉዳዮች ምንም እንኳን ግላዊ ቢሆኑም ጋዜጠኞች ዜናና ፕሮግራሞችን ሲያቀርቡ በተለይ የቀጥታ ስርጭቶች ላይ ጥንቁቅ እንዲሆኑና እጅግ ከፍ ያለ የሙያ ስነ ምግባር ሊያሳዩ እንደሚገባ በመታመኑ ሲሆን ጋዜጠኞች በቀጣይነት በሚሰሯቸው ፕሮግራሞች ላይ ጥንቃቄ እንዳይለያቸው ለማሳሰብ ጭምር እንደሆነ ከስምምነት ላይ ደርሷል።

ሆኖም ምክር ቤቱ ለላከው ደብዳቤ ቅሬታ የቀረበበት ጋዜጠኛ በምክር ቤቱ የአሰራርና የስነ ምግባር መመሪያ 001/15 መሠረት ቀጥተኛ ምላሹንና ማብራሪያውን በጣቢያው በኩል ከመስጠትና በዝግ በሚደረገው ውይይት ላይ ከመሳተፍ ይልቅ ደብዳቤውን በግል የማህበራዊ ሚዲያዎቹ ላይ በመለጠፍና ከምክር ቤቱ ዓላማ ፍላጎትና አካሄድ በተቃራኒ የማህበራዊ ሚዲያ የስም ማጥፋት ዘመቻ መጀመሩ ከፍ ያለ የስነ ምግባር ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል ብሏል። ከዚህም አልፎ በህግ አግባብ የተመሠረተውንና ከ120 በላይ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት፤ የጋዜጠኞች ሙያ ማህበራት፤ የማህበረሰብ ሚዲያዎችና የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን በፍቃደኝነት ያቋቋሙትን ምክር ቤት ‹ምክር ቤቱ ምን ስለሆነ ነው የሚጠይቀኝ?›

ከማለትም አልፎ ቅሬታውን ከተራ የጋዜጠኝነት የሙያ ስነ ምግባር ጥሰት በላይ በማናር ኃይማኖታዊ ይዘት ለመስጠት የሄደበት ርቀት ፈፅሞ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቋል።

ከዚህም አልፎ ጋዜጠኛው የፈፀመው ኢ-ስነ ምግባራዊ ድርጊት የምክር ቤቱን ክብር የሚነካ መሆኑን በማጤን ጣቢያው የወሰደውን አስተዳደራዊ የእግድ እርምጃ የምክር ቤቱ ውሳኔ በማስመሰል የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻና ቅስቀሳ መክፈቱ ምክር ቤቱ በመገናኛ ብዙኃን አዋጅ 1238/13 የተሰጠውን ኃላፊነትና በህዝብ ዘንድ ያለውን የእርስ በእርስ ቁጥጥር ስርዓት ተአማኒነት የሚሸረሽር ነው።

በመሆኑም የኢትየዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤትን በተመለከተ ጣቢያው ማብራሪያ የተጠየቀበትን ደብዳቤ ለግል ዝና ፍጆታ በማዋል የምክር ቤቱን ስም ለማጉደፍ የሄደበትን ርቀት ወደ ስራ በሚመለስበት ወቅት (በጣቢያው አስተዳደራዊ ውሳኔ ወደ ስራው የሚመለስ ከሆነ) የምክር ቤቱን መልካም ስም እንዲያርም፤

በጣቢያ የተወሰደውን አስተዳደራዊ የእግድ እርምጃ ምክር ቤቱን የማይመለከት ውሳኔ መሆኑን እያወቀ ያስተላለፈውን የተሳሳተ መረጃ እንዲያስተካክል፤

እንዲሁም ጣቢያው እንደተለመደው እነዚህ የእርምት እርምጃዎች መፈፀማቸውን ተከታትሎ ለምክር ቤቱ እንዲያሳውቅ ወስኗል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት በሥነ ምግባር የታነጸ በሃላፊነት ስሜት ህዝብን የሚያገለግል ሚዲያ በሀገራችን እንዲጎለብት የሚሰራ ተቋም ሲሆን፤ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ 1238/2013 መሠረት በሕግ ተመዝግበው ፈቃድ የወሰዱ ከ120 በላይ የህዝብ፤ የንግድ፤ የማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃንን፤ የበይነ መረብ ሚዲያንና የጋዜጠኞች ሙያ ማህበራትን በአባልነት በማቀፍ የእርስ በእርስ የቁጥጥር ስርዓትን ተግባራዊ እያደረገ የሚገኝ ተቋም ነው፤

ምክር ቤቱ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት የተላለፉ ዜናዎች፤ ፕሮግራሞችና የማስታወቂያ ስራዎች ላይ የሚታዩ የስነ ምግባር ስህተቶችን ከህዝብ፤ ከመንግስትና ከተለያዩ አካላት ቅሬታ ተቀብሎ በገለልተኝነት የሚመረምርና የጋዜጠኝነትና የሚዲያ ስነ ምግባር እንዲጎለብት የሚሰራ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወጣጣ 18 የበጎ ፈቃደኛ አባላት ያሉት የግልግል ዳኝነት አካል ያለው ሲሆን ከሚዲያ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን በነፃ የስልክ መስመር 6672 ማቅረብ እንደሚቻል ምክር ቤቱ አስታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ምክር ቤት ባለፉት ስድስት ወራት በ5 የንግድ፤ በ4 የህዝብ መገናኛ ብዙኃንና በአንድ የዲጂታል ላይ ከህዝብ የቀረቡትን የስነ-ምግባር ጥሰት ቅሬታዎች መርምሮ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

ስልክ ቁጥር፡ 0115264994 የመ.ሣ.ቁ 14812 ድህረ ገፅ፡ Website; www ethiopianmediacouncil.org
Tel. 0951177273 ጋ 6672 P.O.Box ኢ-ሜይል፡ Email; etmediacouncil@gmail.com;